# እቺን ስም አይጠሪ

አበው እንደሚሉት ፣ ካረጁ አይበጁ
ሞት አድብቶ እያለ ፣ ቆሞላት ከደጁ
ወድቃ እያየናት ፣ ፊቷ ቆሞ አራጁ
ምናል ባትዘባርቅ ፣ ቢሆን በየፈርጁ
ለካስ ቀልብ ያስታል ፣ ግምኛ ሲጃጁ ።

ሞት አፋፍ ላይ ቆማ ፣ የንግዴ ልጅ ውርጃ
በስተመጨረሻ ፣ መቃብር መውረጃ
እንደቀድሞ መስኳት ፣ ህዝቡ መቀለጃ
ንሰሃ እንዳትገባ ፣ ይዛ መማለጃ
ዛሬም ይዳዳታል ፣ ልታዝል ጠብመንጃ ።

በደልና ግፏ ፣ መቼም አያበቃ
ውሃና መብራቱን ፣ አርጋ በፈረቃ
መከራና ስቃይ ፣ ስታደርስ ሰቆቃ
ስትገል ስትዘርፍ ፣ ከህዝብ ተደብቃ
አገር ተራቆተ ፣ በጠፍ በጨረቃ
ምናለ ብትሞት ፣ አርጅታለች በቃ
ሞትም ቢፀየፋት ፣ በገዛ እጇ ታንቃ ።

ዲያቢሎስ አኝኮ ፣ የተፋት አላምጦ
ከርሷ እማይጠረቃ ፣ ያገኘውን ውጦ
አይኖቿም ሞጭሙጨው ፣ ወገቧ ጎባብጦ
ፊቷ ተጨማዶ ፣ ሆዷ ብቻ ፈጥጦ
በለመደው እጇ ፣ ካዝናው ተሟጥጦ
እሷ ስትፈነጭ ፣ ህዝብ ያያል አፍጥጦ
ምነው አይነሳ ፣ በጀግንነት ቆርጦ
ከየጉራንጉሩ ፣ አሮጊቷን መርጦ
በመግቢያ መውጫዋ ፣ አስልቶና አድፍጦ
ሲጥ አርጎ ቢገላት ፣ እስስቷን ጨብጦ ።

በገንዘብ በስልጣን ፣ ተንጀባራ ሰክራ
እግሯም ተሸብቦ ፣ ደግፏት ከዘራ
ደም ብዛት ስኳሩ ፣ ቀስፏት ጨጓራ
ያስጠነቆለችው ፣ ዛር ሞቶባት ከስራ
ዛሬም በስተርጅና ፣ መርዟን ልትዘራ
ታውደለድካለች ፣ ያሮጊት መንጃራ
ምነው የማንድራት ፣ ለጭንቅ ለመከራ ።

በችጋር ተረግዛ ፣ የወለዳት ጠኔ
ከፋሽስት የባሰች ፣ በግፍ በጭካኔ
ህሊና የሌላት ፣ ሁሌ እምትል እኔ
ይብላኝ ለወለደሽ ፣ የምታሰኚ መጥኔ
እቺን ስም አይጠሪ ፣ አሮጊት ወያኔ
ምናምንቴ ነገር ፣ ጨካኝ አረመኔ
ምሰን እንቅበራት ፣ ይምረርህ ወገኔ
ቢገኳት ፅድቅ እንጂ ፣ አይሆንም ኩነኔ ።

ታዛቢው

June 12, 2018